

# የሜሪላንድ የጤና ባለሙያዎች ለጤናማ አየር ንብረት

## የአየር ንብረት ለውጥ ለጤናችን አደገኛ ነው: የሜሪላንድ ጠቅላላ መረጃ

የአየር ንብረት ለውጥ እዚህና አሁን በጤናችን ላይ ተጽእኖ እየፈጠረ ነው። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚባባሱ ጎጂ ተጽእኖዎች የልብና ሳንባ በሽታዎች መጨመርን፣ አሉታዊ የእርግዝና ውጤቶችን፣ ከሙቀት ጋር ተያያዥ ህመሞችን፣ ተላላፊ በሽታዎችን፣ ምግብ ወለድ ህ3መሞችን እና የአእምሮ ጤና እክሎችን ያጠቃልላሉ። በተጨማሪም በተደጋጋሚ ከባድ የአየር ጠባይ መለዋወጦችና የሀይል መቋረጦች ወቅት እንክብካቤ ማግኘት ሊስተጓጎል ይችላል።

### በሜሪላንድ ውስጥ የአየር ንብረት ተጽእኖዎች እና ተጋላጭነቶች:



**ከ3,000 ማይሎች በላይ ርዝመት ያለው የባህር ዳርቻ**

**4ኛው በባህር ወለል ከፍታ መጨመር ምክንያት እጅግ ተጋላጭ ግዛት**



**በተለይም በቀጣዮቹ 30 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የሙቀት፣ እርጥበትና ድርቅ ስጋት**



**በ 2021 የሙቀት መጠኑ በ1970 ከነበረው በ 3.2 ዲግሪ መጨመር**

**በ2050: በ105+ ዲግሪ የሙቀት ጠቋሚ ወደ ~50 ቀናት/ዓመት ለመሆን በማምራት ላይ**

ሜሪላንድ ከባህር ዳርቻ ጀምሮ በምዕራባዊ ሜሪላንድ እስካሉት ተራራዎች ድረስ የተለያየ አይነት የመሬት አቀማመጥ ያለው ሲሆን ሁሉም እነዚህ ለአየር ንብረት ለውጥ ልዩ ተጋላጭነቶች አሏቸው። ሰዎች የከተማ የሙቀት ደሴትነት ተጽእኖን የሚያዩባቸው ሰበሰዎች የተጨናነቁ ከተሞች እና በሰብል ማብቀያ ወቅት እና ሙቀት በከፍተኛ ደረጃ በሚጨምርባቸው ወቅቶች ለለውጦቹ ምላሽ የሚሰጥ ጤናማ የግብርና ዘርፍ አለ። ባልቲሞር ማዕበል በሚያጋጥምበት ወቅትና ከዚያ በኋላ እና ወደ ከተማ ማዕከላት ከባድ ጎርፍ በሚመጣበት ወቅት ከፍተኛ በጎርፍ መጠቃት ያጋጥመዋል።

ለአየር ንብረት ለውጥ ዋነኛ አስተዋጽኦ አድራጊዎቹ የቅሪተ አካል ነዳጆች ለሀይል መቀጣጠር፣ መጓጓዣ እና ኢንዱስትሪ ናቸው። የሚቀጣጠሉ የቅሪተ አካል ነዳጆች የአየር ንብረት እንዳይረጋጋ በማድረግ እና በሚያስከትሏቸው ብክለቶች ምክንያት የጤና አደጋዎችን ይጨምራሉ። እንደ ኦዞን እና PM2.5 አይነት በካዮች የአየር ጥራትን ያራቁታሉ፣ ለተለያዩ አይነት የጤና ችግሮች አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። በቅሪተ አካል ነዳጅ ማቀጣጠያ ተቋማት አቅራቢያ የሚገኙ የሜሪላንድ ነዋሪዎች አካባቢያዊ የአየር ብክለት እንዲሁም ረጅም ርቀት ሊጓዝ የሚችል የሰደድ እሳት ተጽኖዎች ያጋጥሟቸዋል። ለተወሰነ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ መጋለጥ ለልብ በሽታ የስጋት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ዋነኛ የሞት መንስኤ ነው (EPA)።

### ይሳተፉ!

የሜሪላንድ የጤና ባለሙያዎች የአየር ንብረት ቀውስን የሚፈቱ ፖሊሲዎች ላይ ቅስቀሳ ለማድረግ እና የማህበረሰባችንን ደህንነት ለመጠበቅ ልዩ እድል አላቸው።

የሚከተሉትን ጨምሮ ብዙ የጤና ቡድኖች የአየር ንብረት ለውጥ የጤና አደጋ እንደሆነ በይፋ አውጀዋል፡

- የአሜሪካ የህጻናት ህክምና አካዳሚ
- የአሜሪካ የሀኪሞች ኮሌጅ
- የአሜሪካ የህክምና ማህበር
- የአሜሪካ የህዝብ ጤና ማህበር

በሜሪላንድ ውስጥ የሚገኙ የጤና ሙያተኛ ቅንጅት ህዝቡን ለማስተማር እና ጠንካራ ፖሊሲዎችን ለመደገፍ እየሰራ ይገኛል። እርስዎም ያስፈልጉናል.

ከ marvlandclimateaction.com/climate-action-for-health-professionals ላይ ተጨማሪ ይወቁ።

**እንደ እድል ሆኖ ሜሪላንድ የአየር ንብረት መፍትሄዎች መንገድን በመከተል ላይ መሪ ነው። በአገሪቱ እጅግ ባለራዕይ የግሪን ሀውስ ጋዝ ልቀቶችን የመቀነሻ (በ2031 በ60%) ግቦች ያሉን ሲሆን ገዥው ሙር በ2035 ዓ.ም 100% ሪንዱህ ሀይል ለማመንጨት፣ የጸሀይና የንፋስ ሀይልን የበለጠ የሚያቀርቡ አዲስ ህጎችን ለማውጣት በትራንስፖርቱ ዘርፍ የቅሪተ አካል ነዳጅ ብክለትን የሚቀንሱ ጠንካራ ደንቦችን ለመደንገግ በትጋት እየሰሩ ነው።**

# ጠቃሚ ህዝቦች

ተጋላጭነት እና ባላቸው ለአየር ንብረት ስጋቶች ምላሽ የመስጠት አቅም የተነሳ ያልተመጣጠነ ተጽኖ ያጋጥማቸዋል። እነዚህ የህዝብ ክፍሎች ህጻናትን፣ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎችን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶችን፣ በቆዳ ቀለም የተለዩ ማህበረሰቦችን፣ አነስተኛ ሀብት ያላቸው ማህበረሰቦችን፣ አካል ጉዳተኛና ሥር የሰደዱ የጤና እክሎች ያሉባቸው ሰዎችን፣ እና የገጠር የባህር ዳርቻና ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች የመሳሰሉ ለአየር ንብረት ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎችን ያጠቃልላሉ። የአንዳንዶቹ እነዚህ ተጋላጭነቶች ምክንያቶች ያልተመጣጠኑ ማህበራዊ መዋቅሮች እና ለእድሎች ተደራሽ ያለመሆን ናቸው። የሚከተሉት ምሳሌዎች የአየር ንብረት ለውጥ በተወሰኑ የህዝብ ክፍሎች ጤና ላይ የሚያስከትላቸውን ያልተመጣጠኑ ተጽእኖዎች ያብራራል።



ነፍሰ ጡር ሰዎችና ህጻናት

*ሁሉም ህጻናት ለማደግ እና ለመጎልበት ለደህንነት አስተማማኝ እና ጤናማ አካባቢ ማግኘት ይገባቸዋል እንዲሁም ያስፈልጋቸዋል። ህጻናቱ የሚተነፍሱት ጤናማ አየር፣ የሚጠጡት ንጹህ ውሀ፣ የሚመገቡት የተመጣጠነ ምግብ እና የሚኖሩበት፣ የሚማሩበትና የሚጫወቱበት ጤናማ ቦታ ያስፈልጋቸዋል። ይህ በተጨማሪም በአካላቸው ላይ የሚፈጠረው ተጨማሪ ጫና ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ላላቸው ተጽእኖዎች የበለጠ ተጋላጭ ሊያደርጋቸውና በወሊድ ውጤቶች ላይ ተጽእኖ ሊፈጥርባቸው የሚችል በመሆኑ ምክንያት lለነፍሰ ጡር ሴቶችም ያስፈልጋቸዋል።*

**ጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት ከአዋቂዎች ይልቅ ከአካላቸው መጠን ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ የበለጠ የሚተነፍሱ፣ የሚመገቡ እና የሚጠጡ በመሆኑ እና አካላቸውና አንጎላቸው እያደገ የሚሄድ በመሆኑ ምክንያት ለአካባቢ ተጋላጭነቶች በልዩ ሁኔታ ይጋለጣሉ።**

የሚከተሉት ለህጻናት በልዩ ሁኔታ ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው አደጋዎች ናቸው፡

- የሜሪላንድ ህጻናት ከፍተኛ ሙቀት በሚያጋጥምባቸው ቀናት እና ከፍተኛ የመሬት ወለል ኦዞን መጠራቀምን ጨምሮ የውጪው አየር ጥራት ዝቅተኛ በሚሆንበት ወቅት የአስም በሽታ የሚባባስ በመሆኑ ምክንያት ትምህርት ቤት የማይሄዱ ሲሆን አሳዳጊዎቻቸውም ወደ ስራ አይሄዱም። ወደ 53% የሚጠጉት የሜሪላንድ ህጻናት የሚኖሩት የኦዞን ብክለትን መቆጣጠር በማይቻልባቸው ወይም መቆጣጠር ከተቻለ ከሶስት ዓመት ያነሰ ዳታ ባለባቸው ካውንቲዎች ውስጥ ነው።

- ጨቅላ ህጻናት፣ ታዳጊዎች እና በእድሜ ከፍ ያሉ ህጻናት የሙቀት መቆጣጠር አቅማቸው ያልበሰለና ውጤታማነቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ለከፍተኛ ሙቀት የበለጠ ተጠቂ ይሆናሉ።

- ከፍተኛ ሙቀትና ከፍተኛ የአየር ብክለት ያለ ጊዜ መወለድን፣ ዝቅተኛ የወሊድ ወቅት ክብደትን እና የሞተ ህጻን መወለድን ጨምሮ ለአሉታዊ የወሊድ ውጤቶች አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

- የአየር ንብረት ለውጥ የቤተሰብና ማህበረሰብ መረጋጋትን በማስተጓጎል የእንክብካቤ ተደራሽነትን በመቀነስ እና የደህንነትና ምቾት ስሜትን በማሳነስ ወደ ከፍተኛ የአእምሮ ጤና ጫናዎች ሊወስድ ይችላል።

- ነፍሰ ጡር እና የወለዱ ሴቶች አደገኛ የአየር ንብረት ሁኔታዎች ማጋጠምን ተከትሎ ከፍተኛ የPTSD እና የአእምሮ ጤና ተጽእኖዎች ስጋት ስጋት ያጋጥማቸዋል።

- የመሰረተ ልማቶች መስተጓጎል የመጠጥ ውሀን በፍሳሽ በመበከል ለንጹህ ውሀ ተደራሽነትን ሊገድብ እና ወደ ተላላፊ በሽታዎች ሊመራ ይችላል።

- ሞቃት አየር ንብረት በሽታ ተሸካሚ አስተላላፊዎች እንዲስፋፉና የቆይታ ጊዜያቸው እንዲረዝም ሊያደርግ ይችላል፤ ለምሳሌ፡ የላይም በሽታን የሚያሰራጩ መዥገሮች ወይም የወባ በሽታን የሚያሰራጩ የወባ ትንኞች እና ያልተወለደ ህጻንን የሚያጠቃው የዚካ ቫይረስ።



**አካል ጉዳተኛ እና/ወይም ስር የሰደዱ የጤና እክሎች ያሉባቸው ሰዎች**

**የማህበረሰቦቻችን ነዋሪዎችን በርካታ የተለያዩ የሚታዩና የማይታዩ አካል ጉዳቶች እና ሥር የሰደዱ የጤና እክሎች ያጋጥሟቸዋል። የሚያጋጥሟቸው አንዳንዶቹ ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግዳሮቶች የሚከተሉት ናቸው፡**

- የማየት፣ መስማት ወይም የመረዳት ችሎታ እክሎች ያሉባቸው ሰዎች ስለ እጅግ አስቸጋሪ የአየር ጠባይ ሁኔታዎች እና የደህንነት ድጋፎች በተመለከተ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን መረጃ በማግኘት ረገድ የበለጠ ተግዳሮቶች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ።

- አንዳንድ አካል ጉዳተኛ ሰዎች ማቀዝቀዣ ማዕከላትን እና መጠለያዎችን ማግኘት ከባድ የሚሆንባቸው ሲሆን እነዚህ አገልግሎት መስጫዎችም ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ሊቸገሩ ይችላሉ።

- እንደ ከመጠን ያለፈ ተጠራጣሪነት ወይም የመሰላቸት እክሎች የመሳሰሉ የአእምሮ ጤና እክሎች ያሉባቸው ሰዎች ወደ መጠለያ መሄድን ከባድ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።

- የአእምሮ በሽታ መድሀኒቶችን የሚወስዱ ሰዎች ከመጠን በላይ የሆነ ሙቀት በሚያጋጥምበት ወቅት የበለጠ በሙቀት ምክንያት ለሚያጋጥም ስትሮክ እና ለሌሎች ከሙቀት ጋር ተያያዥ ህመሞች ይጋለጣሉ።

## የተወሰኑ የህዝብ ክፍሎች ባልተመጣጠነ ተጋላጭነት እና ባላቸው ለአየር ንብረት ስጋቶች ምላሽ የመስጠት አቅም የተነሳ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ ይደርስባቸዋል።

**ሜሪላንድ ውስጥ በግዛቱ ውስጥ በጠቅላላ ወደ 350,000 የሚጠጉ ሰዎች በግብርና ስራዎች ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ሲሆኑ ወደ 20,000 የሚጠጉ ሰዎች በግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ናቸው። በእነዚህ እና በሌሎች ከቤት ውጭ በሚሰሩ ሙያዎች ላይ የተሰማሩ ሰዎች በሙቀት መጠን መጨመር የተነሳ ልዩ ስጋት ያጋጥማቸዋል። ይህ በተለይም ሰራተኞቹን ለመከላከል የሚያስችሉ ምንም ጠንካራ ደንቦች ወይም የሰራተኛ ደረጃዎች ባለመኖራቸው ምክንያት ነው።**

**በቢሮ ህንጻዎች እና መጋዘኖች ውስጥ ያለው የቤት ውስጥ አየር ጥራትም በውጪው አየር ጥራትና የሙቀት መጠኖች የተነሳ ተጽእኖ ይፈጠርበታል።**

**ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተጽእኖዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:**

- የእርሻ ሰራተኞች ከሌሎች ሰራተኞች ይልቅ በሙቀት ጫና ምክንያት የመሞት እድላቸው በ20 እጥፍ የበለጠ ነው።



**ሰራተኞች**

- የተለየ የቆዳ ቀለም ያላቸው ሰራተኞች በተለይም ሂስፓኒክ ሰራተኞች ለእጅግ ከፍተኛ ሙቀት ያልተመጣጠነ ተጋላጭነት ያጋጥማቸዋል። ሂስፓኒክ የማህበረሰብ አባሎች ምንም እንኳን ከዩኤስ የሰራተኛ ሀይል ውስጥ የሚወክሉት ድርሻቸደ 17% ያክሉን ብቻ ቢሆንም ከ2010 ጀምሮ አንድ ሶስተኛውን በሙቀት ምክንያት የሚያጋጥሙ የህይወት ህልፈቶችን ድርሻ ይወስዳሉ።

- ከቤት ውጭ የሚሰሩ ሰራተኞች እንደ ኦዞን፣ ጭስና ካርቦንዳይኦክሳይድ ለመሳሰሉ የውጭ የአየር ብክለቶች የበለጠ ተጋላጭ በመሆናቸው ምክንያት የበለጠ የመተንፈሻ አካል ህመሞች ስጋት ያጋጥማቸዋል።



## የተለየ የቆዳ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች

**የአየር ንብረት ለውጥ በቀለም የተለዩ ሰዎችን ጨምሮ በተገለሉ ማህበረሰቦች ላይ ያልተመጣጠኑ ተጽእኖዎችን የሚያስከትል መሆኑ አሁን ያለውን እኩልነት አለመኖር ያባብሰዋል። እነዚህ ማህበረሰቦች የአካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ አለመመጣጠኖችን ጨምሮ ከአሰራር ስርዓት ሁኔታዎች ጀምሮ ልዩ ተግዳሮቶች የሚያጋጥሟቸው መሆኑ ይህ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነታቸውን ይጨምረዋል።**

- ሜሪላንድ ውስጥ አፍሪካ አሜሪካውያን እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ማህበረሰቦች ለኢንዱስትሪ የአየር ብክለት ምንጮች የበለጠ በቅርበት የሚኖሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለብክለቶች ተጋላጭ በመሆናቸው ምክንያት ከፍተኛ የካንሰር ስጋት፣ የአስምና የልብ በሽታዎች ያጋጥሟቸዋል።

- በሜሪላንድ ውስጥ የሚኖሩ ሂስፓኒክና አፍሪካ አሜሪካውያን ነዋሪዎች ከግዛቱ አማካኝ ጋር ሲነጻጸር ከትራንስፖርት ጋር ተያያዥነት ካላቸው ልቀቶች ለሚወጣ የንጥረ ነገርም ጥርቅም 2.5 ብክለት ከ10% በላይ ይጋለጣሉ።
- የከተማ ጎርፍ ለአናሳ ማህበረሰቦች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ነዋሪዎች እና ለአደጋ ዝግጁነት ድጋፎች ተደራሽ ላልሆኑ ነዋሪዎች አደገኛ ከመሆኑም ባለፈ ይህ ለሺጋታም ተጋላጭነትን ሊጨምረው ይችላል።

# የአየር ንብረት ለውጥ የጤና ተጽእኖዎችን መፍታት

**የአየር ንብረት በሁሉም የሜሪላንድ ነዋሪዎች ላይ የሚያስከትላቸውን ተጽኖዎች በተለይም በፖሊሲ አማካኝነት ለመከላከልና ለማቅለል አስፈላጊ የአሰራር ስርዓት ለውጦችን በማምጣት ረገድ ሁላችንም ሚና ልንጫወት የምንችል ሆኖ የሚከተሉትን ለማድረግ እርምጃዎችን መውሰድ እንችላለን፡**

- የአካባቢ ባለስልጣናትን ግንዛቤ በማሳደግ እና የአካባቢና የጤና አለመመጣጠኖችን የሚፈቱ ፖሊሲዎችን እንዲደግፉ በማበረታታት።
- የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ወደነበረበት ለመመለስ አረንጓዴ ቦታዎችን በመጠበቅና በማዘጋጀት እና ከማህበረሰብዎ ጋር በማገናኘት።
- እንደ ብስክሌት፣ የእግር ጉዞ እና የህዝብ ትራንስፖርት የመሳሰሉ ዘላቂና ፈጣን የትራንስፖርት ሞዴሎችን በመደገፍ።
- በታሪክ ውስጥ ከአየር ንብረት መፍትሄዎች የተገለሉ ግለሰቦችን ለመደገፍ ቅስቀሳ በማድረግ።
- ለማህበረሰቡ ታዳሽ ሀይልና ሀይል ቆጣቢ ዘዴዎችን እንዲጠቀም በማስተዋወቅ።

**የሚከተሉት ድርጅቶች ለዚህ የመረጃ መስጫ ቅጽ አስተዋጽኦ አድርገዋል:**